የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ–ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 13
ADDIS ABABA - 24th Nov., 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፮/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
ለግልገል ጊቤ ኃይድሮ ኤሌክትሪክ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...................... ገጽ ፰፻፺፯

## CONTENTS

Proclamation No. 136/1998
European Investment Bank Finance Contract for financing the Gilgel Gibe Power Plant Project Ratification Proclamation .................. Page 897

### አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፮/፲፱፻፺፩
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለግልገል ጊቤ ኃይድሮ ኤሌክትሪክ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኢኪው ፵፩ ሚሊዮን (አርባ አንድ ሚሊዮን ኢኪው) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር ፩ ቀን ፲፱፻፺፰ በሉግዘምበርግ የተፈረመ በመሆኑ ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለግልገል ጊቤ ኃይድሮ ኤሌክትሪክ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፮/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION 136/1998
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCE CONTRACT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EUROPEAN INVESTMENT BANK

WHEREAS, a Finance Contract, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the European Investment Bank stipulating that the European Investment Bank provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of ECU 41,000,000 (forty one million ECU) for financing the Gilgel Gibe Power Plant Project, was signed in Luxembourg, on the 1st day of september, 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Finance Contract at its session held on the 24th day of November, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "European Investment Bank Finance Contract for Financing the Gilgel Gibe Power Plant Project Ratification Proclamation No. 136/1998."

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴሬላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል ሴፕቴምበር ፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. በሉግዘምበርግ የተፈረመው ቁጥር ኤፍ ፩ ኤን ኦ ፯–፩ሺ፩፻፲፬ የብድር ስምምነት ነው ፡፡

፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኢኪው ፵፩ ሚሊዮን (አርባ አንድ ሚሊዮን ኢኪው) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ፡፡

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Finance Contract" means the Finance Contract No. F1 No. 7-1114, signed in Luxembourg on the 1st day of September, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the European Investment Bank.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilisation of the credit amount of ECU 41,000,000 (forty one million ECU) in accordance with the terms and conditions set forth in the Finance Contract.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 24th day of November, 1998.

Done at Addis Ababa, this 24th day of November, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE